# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

## ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

## MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

## OF THE CENTERAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

ወልቂጤ 4ኛ ዓመት ቁጥር 16
ሐምሌ 18/ 2016 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የህዝብ
ተወካዮች ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

Wolikite 4th Year No 16
July, 25/2024


## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሀብት ማሣወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 16/2016 ዓ.ም

### መግቢያ

ሀብትን ማሣወቅና ማስመዝገብ የመንግስት አሠራርን በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሀብት ማሣወቅና ማስመዝገብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

የመንግስት የሥራ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሣይቀላቀሉ በየራሣቸው መንገድ የሚመሩበትን

## Proclamation No. 16/2024

## A Proclamation to Provide for the Disclosure and Registration of Assets of the Central Ethiopia Region State

### PREAMBLE

**WHEREAS**, the disclosure and registration of assets is paramount importance in the prevention of corruption and impropriety and helps to enhance good governance based on transparency and accountability;

**WHEREAS**, the disclosure and registration of assets is of paramount importance in the prevention of corruption and impropriety and helps to enhance good governance;

**WHEREAS**, it is necessary to put in place a transparent system that would help the conduct

ግልጽ ስርዓት መዘርጋት ሊፈጠር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለማስወገድ እንደሚረዳ በመታመኑ፤

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ **"የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሀብት ማሣወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 16/2016 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. **"ክልል"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው፣
2. **"ምክር ቤት"** ማለት የክልል፣ የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር ህግ አውጪ የመንግስት አካል ነው፣
3. **"መስተዳድር ምክር ቤት"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል ነው፣
4. **"ብሔረሰቦች ምክር ቤት"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የብሔረሰቦች ምክር ቤት

of public affairs and private interest go separate without intervening into one another's territory so as to avoid possible conflict of interest;

**Now, Therefore,** according to Article 55 sub-Article 3 of the Constitution of the Central Ethiopia Region State, the following is proclaimed.

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the **"Disclosure and Registration of Assets of Central Ethiopia Region State Proclamation No. 16/2024."**

2. **Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. **"Region"** means the region of Central Ethiopia;
2. **"Council"** means the legislative body of Region, zonal, special wereda, wereda and city administration;
3. **"Executive Council"** means the executive body of the Central Ethiopia Region government;
4. **"Council of Nationalities"** means the Council of Nationalities of the Central

ነው፣

5. **“አስተዳደር ምክር ቤት”** ማለት በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር የሚገኝ የህግ አስፈፃሚ አካል ነው፣

6. **“ሀብት”** ማለት ማንኛውም የማይንቀሣቀስ ወይም የሚንቀሣቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታን እና ዕዳን ይጨምራል፣

7. **“ኮሚሽን”** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡

8. **“የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል”** ማለት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ሥነ-ምግባርን ለማስፈን፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል በሥነ ምግባር ኦፊሰር የሚመራ የሥራ ክፍል ነው፣

9. **“ተሿሚ”** ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) በክልል፣ በዞን ፣በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ እና በከተማ ምክር ቤቶች ቀርበው የተሾሙትንና የሚሾሙትን ፤

ለ) በክልል መስተዳድር ምክር ቤት እና በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማ የአስተዳደር ምክር ቤቶች ቀርበው

Ethiopia region;

5. **"Administrative Council"** means a legal executive body in the region, zonal, special wereda, wereda and city administration;

6. **“Asset”** means any movable or immovable or tangible or intangible property and includes landholdings and debts;

7. **“Commission”** means the Central Ethiopia Region State Ethics and Anti-Corruption Commission;

8. **“Ethics liaison unit”** means a work unit headed by an ethics expert (officer) to establish ethics in government offices or government development organizations, to prevent corruption and malpractice.

9. **“Appointee”** includes the following:

a) Those persons appointed or to be appointed by the Regional, zonal, Special Wereda, Woreda, and City Councils on recommendation;

b) Those persons appointed or to be appointed by the Region Administrative Council, Zonal , Special wereda, Woreda

የተሾሙትንና የሚሾሙትን

ሐ) በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳና በወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች እና በከተማ ከንቲባ ቀርበው የተሾሙትንና የሚሾሙትን

መ)በክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት ቀርበው የተሾሙትንና የሚሾሙትን

ሰ)በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን እና ስራ አስኪያጆችንና ምክትል ስራ አስኪያጆችን፣

10. **"የመንግስት ሠራተኛ"** ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

ሀ/ፈቃድ የመስጠት፤ የመቆጣጠር፤ ገቢ የሚሰበስቡና የሚወስኑ፤ ግዥ የመፈጸም ወይም የከተማ መሬት የማስተዳደር ስራ የሚያከናወኑ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች፤ ዓቃቤ ሕጎችን፤ መርማሪዎችን፤ የትራንስፖርት ፍሰት ተቆጣጣሪዎችን እና

ለ/ ኮሚሽኑ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ተለይተው የሚወሰኑ ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና መንግስት የልማት ድርጅቶች ሰራተኞች፤

and Urban Councils on recommendation;

c) Those persons appointed or to be appointed by the Chief Executive of the Region as well as the Chief Administrators of the Zonal, Special Wereda, Woreda Administrations and City Mayors on recommendation;

d) Those who have been appointed and will be appointed by the Council of Nationalities of the region;

e) Members of Board of Directors, Managers and Deputy Managers of Public Enterprises;

10. **"Public Servant"** includes the following:

a) public office directors, employees, prosecutors, judges, office managers, department heads, work process coordinators, inspectors, traffic flow controllers and, who carry out the work of licensing, controlling, collecting and determining revenue, making purchases or managing urban land;

b) Employees of other government offices and government development organizations determined by the regulation or directive issued by the commission;

11.**“ቤተሰብ”** ማለት የተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ ወይም በስሩ የሚተዳደር ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ልጅ ሲሆን ጋብቻ ሣይፈጽም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የሚኖር ሰውን እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል፣

12.**“የቅርብ ዘመድ”** ማለት የተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ወላጆችን፣ ተወላጆችን፣ እህቶችን፣ ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፣

13.**“የመንግስት መስሪያ ቤት”** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደርና የሕግ አውጭነት፣ የዳኝነት ወይም አስፈፃሚነት የመንግስት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣

14.**“የመንግስት ልማት ድርጅት”** ማለት የክልል መንግስት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክስሲዮን ኩባንያ ነው፣

15.**“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

16.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አነጋገር

**11.** “**Family**” means the spouse or a dependent child, under the age of 18, or an appointee, elected person or a public servant and include a person living together under irregular union and an adopted child;

**12. “Close Relative”** includes ascendants, descendants, siblings and other persons related to an appointee, elected person or a public servant by consanguinity or affinity up to the third degree;

**13. “Public Office”** means any office the budget of which is fully or partially allocated by government and in which legislative, judicial or executive activities of government are performed;

**14. “Public Enterprise”** means any public enterprise or a share company in which the total or part of the holdings is owned by government;

**15. “Person”** means a natural or juridical person;

**16.** Any expression in the masculine gender

ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና በልማት ድርጅቶች በሚሰሩ ተሿሚዎችና የመንግስት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሀብትን ስለማሣወቅና ስለማስመዝገብ

4. <u>ሀብትን የማሳወቅ እና የማስመዝገብ ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ/ በራሱና በቤተሰቡ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ሥር የሚገኝ ሀብትን እና

ለ/ የራሱንና የቤተሰቡን የገቢ ምንጮች የማሣወቅና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሀብቱን የሚያስመዘግብ ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የራሱንና የቤተሰቡን ሀብትና የገቢ ምንጮች ለየብቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ወይም ሶፍተዌር ላይ ወይም በሁለቱም ላይ በመሙላት ትክክለኛነቱን በፊርማው ያረጋግጣል፡፡

includes the feminine.

**3. Scope of application**

This Proclamation shall apply to appointees and public employees working in region, zonal, Special Wereda, wereda and city administration offices and development organizations.

## PART TWO

## Disclosure and Registration of Assets

**4. Obligation to Disclose and Register of Asset**

1. Any appointee or public servant shall have the obligation to disclose and register:

a) the assets under the ownership or possession of himself and his family; and

b) Sources of his income and those of his family.

2. The appointee or public servant who registers his assets pursuant to sub-article (1) of this Article shall fill the particulars of his assets and sources of income and those of his family in separate forms designed for such purposes or on the software registration system and authenticate the same by his signature.

## 5. በምዝገባ ስለማይካተት ሀብት

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሀብቶች አይመዘገቡም:-

ሀ/በውርስ ተገኝቶ በጋራ የተያዘና ለወራሾቹ የግል አገልግሎት የሚውል ንብረት፣

ለ/ የቤት እቃዎችና የግል መገልገያዎች፣

ሐ/ ከጡረታ የሚገኝ ገቢ፡፡

2. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት በጋራ የተያዘ ንብረት በወራሾች መካከል እንደተከፋፈለ ድርሻውን አሣውቆ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 6. ስለመዝጋቢ አካል

1. የተሿሚዎችንና የመንግስት ሠራተኞችን ሃብት የሚመዘግበው ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተሿሚዎችን ወይም የመንግስት ሠራተኞችን ሃብት እንዲመዘግብ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍልን ሊወክል ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ውክልና የተሰጠው እያንዳንዱ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበለትን የሃብት

## 5. Assets Exempted from Registration

1. Notwithstanding the provisions of Article 4 of this Proclamation, the following assets shall be exempted from registration:-

a) common property acquired through inheritance and held by the heirs for private use;

b) household goods and personal effects;

c) pension benefits;

2. Any appointee or a public servant who has a share in a common property held in accordance with sub-article (1) (a) of this Article shall disclose his share for registration as soon as the property is liquidated among the heirs.

## 6. Body in Charge of Registration

1. The Commission shall register assets of appointee and public servant.
2. The Commission may delegate fully or partially as the case may be Ethics Liaison Unit to register assets of appointee or public servant when it deems it necessary.
3. In accordance with sub-article 2 of this Article, each ethics liaison unit shall send the document of registration of assets submitted to it in accordance with sub-article (2) of Article 4 of this Proclamation to the Commission within

ማስመዝገቢያ ሰነድ ወይም ሶፍትዌር ምዝገባው በተደረገ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል፡፡

4. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ የሀብት ምዝገባ ሰነዶች ጠባቂ ሆኖ ያገለግላል፤ ሀብታቸውን ላስመዘገቡ ተሿሚዎችና የመንግስት ሠራተኞች የምዝገባ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

7. <u>ምዝገባ ስለሚካሄድበት ጊዜ</u>

1. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ከስድስት ወር ቀጥሎ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ሀብቱን ማሣወቅና ማስመዝገብ አለበት፡፡

2. ማንኛውም አዲስ ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ሀብቱን የሚያሣውቀውና የሚያስመዘግበው ከተሾመበት ወይም ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በ45 (አርባ አምስት) ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 መሠረት ሀብቱን ያስመዘገበ ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ከዚያ በኋላ ሀብቱን የሚያሣውቀውና የሚያስመዘግበው በየሁለት ዓመት ተከቦ ሆኖ ይህ ጊዜ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

30 days from the date of registration.

4. The Commission shall be the custodian of documents of registration of assets under this Article, and shall issue certificates of registration to the appointees and public servants whose assets have been registered.

7. **Time of Registration**

1. Any appointee, elected person or public servant shall disclose and register his assets within six months after the six months next to the coming in to force of this Proclamation.

2. Any newly appointed or employed person shall disclose and register his assets within 45 days following his appointment or employment.

3. Any appointee, elected person or public servant who has registered his assets in accordance with sub-article (1) or (2) of this Article shall disclose and reregister the same every two years within 30 days from the end of the budget year.

8. የምዝገባ ጊዜን ስለማራዘም

1. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት የሚጠይቅ ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ምዝገባውን ማራዘም ያስፈለገበትን ምክንያት በጽሁፍ በመግለጽ የምዝገባ ጊዜው በተጠናቀቀ በአምስት ቀናት (5) ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ ምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ማመልከት ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው የሥነ ምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለት ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው የምዝገባውን ጊዜ ለአንድ ጊዜ እስከ 30 (ሠላሳ) ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡
3. የምዝገባ ጊዜ እንዲራዘምለት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት አመልካች ውሣኔው በደረሰው አምስት ቀናት (5) ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፤ ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

9. ዘግይቶ ስለማስመዝገብ

ሀ/በመደበኛው ወይም በተራዘመለት የማስመዝገቢያ ጊዜ ውስጥ ሀብቱን ያላስመዘገበ ተሿሚ ወይም የመንግስት

**8. Extension of Time of Registration**

1. A person demanding an extension of the time of registration may establish the cause for the extension in writing and submit the same to the Commission or to the relevant ethics liaison unit within (5) five days from the expiry of the time of registration.
2. The commission or the relevant ethics liaison unit may, upon ascertaining that the application submitted under sub-article (1) of this Article is based on sufficient cause, extend the time of registration only once for up to 30 days.
3. An applicant whose application for extension of the time of registration is rejected by an ethics liaison unit may apply to the Commission within (5) five days from receipt of the decision of the ethics liaison unit; the decision of the Commission shall be final.

**9. Late Registration**

a) If an appointee, elected person or a public servant fails to register his assets within the normal or extended period of registration, he shall pay a fine of Birr

ሠራተኛ ብር 1000 (አንድ ሺ ብር) መቀጫ ከፍሎ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ሊያስመዘግብ ይችላል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠሰው የጊዜ ገደብ መሠረት ማስመዝገብ ያልቻለ ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በእያንዳንዱ 30 ቀን ተጨማሪ 1000 (አንድ ሺ ብር) መቀጫ የሚከፍል ሆኖ ይህ የመቀጫ ጊዜ ከ3 ጊዜ በላይ ሊራዘም አይችልም፡፡

## 10. ከስንብት በኋላ ስለሚከተሉ ግዴታዎች

ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል ወይም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ሀብቱን በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለሚመለከተው የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል እንዲሁም ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ለኮሚሽኑ ማሣወቅ አለበት፡፡

## 11. የምዝገባን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተሿሚ ወይም በመንግስት ሠራተኛ በተሞላ መረጃ ትክክለኛነትን በራስ ተነሳሽነት ወይም ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ የያዘ መሆኑን ለመጠርጠር በቂ

1,000 (one thousand) and register his assets within 30 days.

b) Subject to the provisions of subsection (a), of this article, an appointee or public employee who fails to register within the given time limit shall pay an additional fine of one thousand birr every 30 days, and this penalty period cannot be extended more than 3 (three) times.

## 10. Post-Employment Obligations

Any appointee, elected person or a public servant who has retired or terminated his service on any ground shall disclose his assets to the Commission or the concerned ethics liaison unit within 30 days from the date of his retirement or termination of service and finally to the commission after two and half years.

## 11. Verification of Registration

1. The Commission shall undertake a verification process on the information submitted by an appointee or a public servant in accordance with sub-article 2 of Article 4 of this Proclamation where it has sufficient ground to suspect the submission of incomplete, inaccurate or

ምክንያት ሲኖረው ወይም ሀብቱ በትክክል አልተመዘገበም የሚል ጥቆማ ሲቀርብ የምዝገባውን ትክክለኛነት የማጣራት ተግባር ያከናውናል፡፡

2. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የማጣራት ተግባር ሲያከናውን፡-

ሀ/ጉዳዩ የሚመለከተው ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው፣

ለ/ የተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛውን ሀብት የሚመለከት መረጃ ያለው ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው መረጃውን እንዲሰጥ ሊያዘው፣ እና

ሐ/የዋና ኦዲተርን ወይም የሌላ አግባብነት ያለውን አካል ሙያዊ ድጋፍ ሊጠቀም ይችላል፡፡

3. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተጠቀሰው መሠረት ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ ወይም የሀሰት መረጃ መቅረቡን በማስረጃ ሲያረጋግጥ ጥፋት በፈጸመው ሰው ላይ በሕጉ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ያደርጋል፡፡

false information or where information is received on the inaccuracy of the registration or a criminal investigation is underway.

2. The Commission may, in the course of verification process under sub-article (1) of this Article:-
   a) May require the concerned appointee or public servant to produce additional information and clarification of the issue;
   b) May order any bank, financial institution or any other person having information regarding the assets of the concerned appointee, elected person or public servant to furnish such information; and
   c) May avail itself of the professional assistance of the Auditor General or any other relevant body.

3. Whenever the Commission ascertains, with evidence, the existence of incomplete, inaccurate or falsified information, in accordance with sub-article 1 and 2 of this article, it shall cause necessary measures to be taken upon the culprit according to the law.

## 12. የምዝገባ መረጃ ተደራሽነት

1. በኮሚሽኑ እጅ የሚገኝ ማንኛውም የተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የሀብት ምዝገባ መረጃ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፡፡
2. ስለሀብት ምዝገባ መረጃ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጥያቄውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የምዝገባውን መረጃ ለጠየቀው ሰው መስጠት አለበት፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የቤተሰብ ሀብትን የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለፍትህ ስራ ወይም ኮሚሽኑ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚወሰነው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር የሚያዝ ይሆናል፡፡
5. ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በየሁለት ዓመት ተከትሎ ስላከናወነው የሀብት ምዝገባ አጠቃላይ መረጃ በሪፖርት መልክ ያወጣል፡፡

## 13. የሀብት አለመመዝገብ የሚያስከትለው ውጤት

በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ ማንኛውም

## 12. Accessibility of Registered Information

1. All information regarding the registration of assets of an appointee or a public servant shall be open to the public.
2. Any person who wishes to access information regarding the registration of assets may apply in writing to the Commission or to the concerned ethics liaison unit.
3. The commission or ethics liaison unit shall give the registration information to the person asked by accepting the request.
4. Notwithstanding the provisions of this Article the information regarding the registration of family assets shall be confidential unless disclosure is required in the interest of justice or for other purposes to be determined by the Commission as necessary.
5. The Commission shall provide the public with general information regarding the registration of assets under this Proclamation every two years by way of reports.

## 13. Effect of Non-Registration of Assets

Any wealth of an appointee or public employee that is not registered according to

የተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ሀብት ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 (2) ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል ምንጩ እንዳልታወቀ ንብረት ይቆጠራል፡፡

this proclamation shall be considered as undisclosed property for the purpose of implementation article 419 (2) of Criminal Code unless evidence to the contrary is provided.

## ክፍል ሶስት
## የጥቅም ግጭትን ስለማሣወቅና ስለማስወገድ

## PART THREE
## Disclosure and Avoidance of Conflict of Interest

### 14. መርህ

ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የያዘውን መንግስታዊ የኃላፊነት ቦታ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ ማዋል አለበት፡፡ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን በስራው አጋጣሚ ያገኘውንና ሕዝብ እንዲያውቀው ያልተደረገን መረጃ ለግል ጥቅሙ ማዋል የለበትም፡፡

### 14. Principle

Any appointee or a public servant shall use the public office to which he is entrusted to protecting the public interest alone. On no account shall he secure personal gain from the information brought to his knowledge as a result of his assumption of public office and not made public.

### 15. ስጦታ፣ መስተንግዶና የጉዞ ግብዣ

1. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የመወሰን ስልጣኑን የሚፈታተን ወይም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ መቀበል የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቀረበለትን ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ያለመቀበል በስራ ግንኙነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስጦታውን፣ መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን

### 15. Gift, Hospitality and Sponsored Travel

1. Any appointee or a public servant may not accept any gift, hospitality or sponsored travel that may put his authority to decide under question or ensue conflict of interest.
2. Notwithstanding sub-article (1) of this Article, if refusal to accept a gift, hospitality or sponsored travel may jeopardize working relation, an appointee, an elected person or a public servant may accept the gift, hospitality or sponsored travel; provided, however, he shall deposit

ለመቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም የተቀበለውን ስጦታ አግባብ ላለው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ገቢ ማድረግ ወይም መስተንግዶውን ወይም የጉዞ ግብዣውን ለኮሚሽኑ ወይም አግባብነት ላለው የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ማሣወቅ አለበት፡፡

16. <u>የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ</u>

1. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በመንግስት የስራ ኃላፊነቱ በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት ሊያስከትልበት የሚችል ጉዳይ ሲያጋጥመው፡-
   ሀ/ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ወይም አስተያየት ከመስጠት እንዲሁም ከኃላፊነቱ ጋር የማይጣጣም ወይም ታማኝነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ማንኛውንም ድርጊት ከመፈጸም መቆጠብ፣ እና
   ለ/ ሁኔታውን ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማሣወቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጥቅም ግጭት ሊከሰት መቻሉ የተገለጸለት የበላይ ኃላፊ እንደሁኔታው ተሿሚው ወይም የመንግስት ሠራተኛው ጉዳዩን ማየቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሊሰጠው ወይም ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል፡፡

the gift with the relevant public office or public enterprise or disclose the hospitality or sponsored travel to the Commission or the relevant ethics liaison unit.

**16. Measures to be Taken to Avoid Conflict of Interest**

1. Where an appointee, an elected person or a public servant encounters a case that may lead to a conflict between his official duty and his own or his close relative's private interest, he shall:
   a) Refrain from giving decision or opinion on the case as well as from taking any action that may be inconsistent with his official duty or may compromise his loyalty; and
   b) Disclose the situation to the concerned higher official.
2. A higher official who has received a disclosure under sub-article (1) of this Article may instruct the appointee or public servant to continue handling the case or may delegate another person instead, as the case may be.

## 17. የጥቅም ግጭትን መከሰቱን ተከትሎ ስለሚወሰድ እርምጃ

ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በመንግስት የስራ ኃላፊነቱና በራሱ ወይም በቅርብ ዘመዱ የግል ጥቅም መካከል ግጭት መከሰቱን ተከትሎ በራሱ ተነሣሽነት ወይም በበላይ ኃላፊው ሲጠየቅ ጥፋተኛ መሆኑን በይፋ አምኖ ይቅርታ የመጠየቅ ወይም ራሱን ከኃላፊነት የማግለል ግዴታ አለበት፡፡

## 18. ከሥራ መልቀቅ በኂላ ስለሚኖር ክልከላ

ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ሥራ በለቀቀ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሲቆጣጠራቸው ከነበረው ሰዎች ጋር ጥቅም የሚያስገኙ ሥራዎች መስራት የለበትም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ወይም በመመሪያ ይገለፃል፡፡

## 19. የጥቅም ግጭትን የማሣወቅ ግዴታን ስላለመወጣት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን በዚህ አዋጅ መሠረት የማሣወቅ ግዴታውን ካልተወጣ አግባብ ባለው የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 17. Measures to be Taken Following the Event of Conflict of Interest

Any appointee, elected person or public servant shall, following any event of conflict between his official duty and his own or his close relative's private interest, publicly admit his fault and ask for apology or resign from office, on his own initiative or when required by his superior to do so.

## 18. Post-Employment Limitation

Any appointee, elected person, or public servant may not take up any benefit ensuing work from persons whom he used to control, until two years after leaving office. The details shall be provided in regulations and/or directives.

## 19. Failure to Disclose Conflict of Interest

An appropriate administrative sanction shall, in accordance with the relevant code of ethics, be taken against any appointee, elected person or public servant who fails to disclose any conflict of interest in accordance with this Proclamation.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ጥቆማ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አወጅ ጥሷል በሚለው ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ላይ ጥቆማ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጥቆማው እስከተቻለ ድረስ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም አግባብ ላለው የስነ ምግባር መከታተያ ክፍል መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. በቀረበው ጥቆማ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የምርመራ ሂደቱና መዛግብቱ በሚስጥር ተይዘው ይቆያሉ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት በቀረበ ጥቆማ የተገኘ መረጃ በወንጀል ህግ አንቀጽ 419 (2) የሀብት መወረስ ውሣኔ የሚያስጥ ከሆነ የተወረሰው ሀብት ከሚያስገኘው ገቢ ውስጥ 25 በመቶ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

### 21. የአዋጁን ተፈፃሚነት ስለማረጋገጥ

ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ፡-

1. ተሿሚዎች ወይም የመንግስት ሠራተኞች ሀብታቸውን በወቅቱ እንዲያስመዘግቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 20. Whistle-blowing

1. Any person may file whistle-blowing against an appointee, an elected person, or a public servant for breaching this Proclamation.
2. A whistle-blowing shall be submitted, in writing, to the commission or the relevant ethics liaison unit and, as much as possible, be accompanied with supporting evidence.
3. The investigation process and related documents shall be kept confidential until final decision is taken on the whistle-blowing.
4. If the information obtained through whistle-blowing leads to the confiscation of assets under Article 419 (2) of the Criminal Code, the whistle-blower shall be entitled to 25% of the proceeds of the confiscated asset.

### 21. Assuring Applicability of the Proclamation

Any public office or public enterprise shall, to ensure compliance with this Proclamation:

1. facilitate the timely registration of assets of appointees, elected persons and public servants;

2. አግባብ ያላቸው የሥነ-ምግባር ደንቦችን አውጥቶ ተፈፃሚ ያደረጋል፡፡

22. ቅጣት

1. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ/ ሀብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ሳያሣውቅ ከቀረ ወይም ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ የምዝገባ መረጃ ከሰጠ ወይም

ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ስጦታ፣ መስተንግዶ ወይም የጉዞ ግብዣ ከተቀበለ ወይም የተቀበለውን ስጦታ፣ መስተንግዶ፣ ወይም የጉዞ ግብዣ ሣያሣውቅ ከቀረ፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 417 መሠረት ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ለኮሚሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ጥቆማ አቅርቧል ወይም ምስክርነት ሰጥቷል ወይም ጥቆማ ለማቅረብ ወይም ምስክርነት ለመስጠት ተዘጋጅቷል በሚል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበቀል እርምጃ የወሰደ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 444 መሠረት ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ተሿሚ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የጥቅም ግጭት መኖሩን

2. Issue and enforce relevant code of ethics.

**22. Penalty**

1. Any appointee or public servant who:

a) fails to disclose his assets for registration in accordance with this Proclamation or intentionally submits incorrect disclosure; or

b) in contravention of this Proclamation, accepts a gift, hospitality or sponsored travel, or fails to disclose any gift, hospitality or sponsored travel he has accepted; shall be punished in accordance with Article 417 of the Criminal Code.

2. Any appointee, elected person or public servant who directly or indirectly takes any reprisal measure against a whistle-blower or witness for submitting whistle-blowing or giving witness or is about to submit whistle-blowing or give testimony to the Commission or ethics liaison unit pursuant to Article 20 of this Proclamation shall be punished in accordance with Article 444 of the Criminal Code.

3. Any appointee, elected person or public servant who, either without disclosing the existence of conflict of interest or acting

ሳያሣውቅም ሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተፈቅዶለት ሲሰራ የመንግስት ኃላፊነቱን ተጠቅሞ የራሱን ወይም የቅርብ ዘመዱን የግል ጥቅም ያራመደ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

4. ማንኛውም ሰው በክፉ ልቦና በመነሳሳት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ጥቆማ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 መሠረት ካቀረበ እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እስራት ወይም እስከ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

### 23. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ህግ ወይም ማንኛውንም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 24. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

upon being authorized in accordance with sub-article (2) of Article 17 of this Proclamation, uses his official duty to promote his own or his close relative's private interest shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

4. Any person who, motivated by bad intentions, makes a suggestion without any basis according to article 20 of this Proclamation, will be punished with imprisonment of up to three years or a fine of up to 2,000 birr (two thousand) or both.

### 23. Inapplicable Laws

No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

### 24. Power to Issue Regulations and Directives

1. Council of the Region may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.
2. The Commission may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

25. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ወልቂጤ**

**ሀምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም**

**እንደሻው ጣሰው**

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት**

**ፕሬዚደንት**

**25. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of its publication on the Region Negarit Gazeta.

**Done at Wolkitie**

**July 25, 2024**

**Endashaw Tasew**

**President of Central Ethiopia Regional State**